# ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
# Re'ese Adbarat Debre Selam Kidest Mariam
# Ethiopian Orthodox Tewahido Church

"እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁአቸው የእኔ ደቀመዝሙር አድርጓቸው "። ማቴ ፳፰፣ ፲፱ *"Therefore go and make disciples of all nations, baptizing them in the name of the Father and of the Son and of the Holy Spirit, "Matthew 28:19*

የር/አ/ደ/ሰ/ቅ/ሚርያም ቤተ ክርስቲያን ጊዜያዊ አመራር የሰላምና መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ
*INTERIM COMMITTEE*

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።
*IN THE NAME OF THE FATHER THE SON THE HOLY SPIRIT ONE GOD AMEN.*

ነሐሴ 10 ቀን 2008 ዓ.ም./Aug 17, 2016/

## የሀገርን ሰላም ፈልጉ (ትንቢተ ኤርምያስ 29፡7)

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘመናትን ተሻግራ እዚህ የደረሰችው በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት በአባቶቻችን ጸሎት እንዲሁም በዜጎቿ ጽኑ አንድነትና ሀገር ወዳድነት መሆኑ ይታውቃል። ሀገራችንን በተለያዩ ዘመናት ለመምራት የተነሡ ነገሥታትና መሪዎች ከህዝቡ ጋራ ከነበራቸው ትሥሥርና ቅን የመምራት ብቃት ህዝቧን በፍቅርና በትህትና ከመምራታቸው ባሻገር ኢትዮጵያን ለመውረር ታሪኳን ለማጥፋት ሕዝቧን ለባርነትና ለቅኝ ግዛት ለመዳረግ የመጡ የውጭ ጠላቶችንም እንኳ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በአንድነት በመቆም ጀግኖች ልጆቿ በከፈሉት መስዋእትነት ድል እየነሳች ያላትን አኩሪ ታሪክ ለትውልድ ለማቆየት ችላለች። ከሀገራችን አልፎም ለአፍሪካውያን ብሎም ለመላው ዓለም የጥቁሮች ነጻነት ምሳሌ የሆነው የአድዋ ድልና ሌሎችም የሀገራችን ታሪኮች የተገኙት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አስተዋጽኦ፤ በቅን መሪዎቿ ብሎም ደግሞ በህዝቡ ሀገር ወዳድነት እና አንድነት መሆኑ ይታወቃል። በሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ብሔረሰቦች ቢኖሩም ቋንቋ ፤ ጎሳ፤ ወንዝ ሳይከፋፍላቸው ከብሔርተኝነት በመራቅ ኢትዮጵያዊነት ከምንም በላይ መሆኑን አምነው በፍቅርና በአንድነት በመቆም የሠሩት ታሪክ ትውልድ ሁሉ ሲዘክረውና ሲኮራበት ይኖራል።

ይህ ብሔራዊ አንድነት ተጠብቆ ሊያዝ ሲገባው በአሁኑ ሰዓት ሀገሪቱን እየመራ የሚገኘው መንግሥት የራሱን ስልጣን ለማጽናትና ዓላማውን ለማሳካት የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎሳ፣ በቋንቋና በብሔር በመከፋፈል በሕብረተሰቡ ውስጥ የመለያየትን እና የጥላቻን ዘር በመዝራት በአባቶቻችን ተጠብቆ ይኖር የነበረውን የሀገርን ፍቅርና የሕዝቡን አንድነት በማጥፋት ዘረኝነት እንዲስፋፋ፤ የጎሳ ግጭቶች እንዲፈጠርና እርስ በእርሱ እንዲጠላላ ምክንያት ሆኗል።

ይህ መንግሥት እየሄደበት ያለው ጉዞ ሀገሪቱ ላይ ሊያስከተል የሚችለውን ከፍተኛ ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሃይማኖት አባቶች፣ ምሁራን፣ እንዲሁም የሀገር ሽማግሌዎች ከጅምሩ በአንድ ድምፅ ባለመቃወማቸው፤ በመመካከርና በህብረት ሀገሪቷን ለመታደግ እርምጃ ባለመውሰዳቸው፤ በተለያዩ ክልሎች እየተፈጠሩ ያሉ የጎሳ ግጭቶች ፤ ኢትዮጵያዊ እንደ ኢትዮጵያዊነቱ ሊያገኝ የሚገባው ሙሉ የዜግነት መብቱ በክልል እንዲወሰን መደረጉ ፤ ከዚህም የተነሳ ዜጎች በጉልበታቸው ያፈሩትን ሀብትና ንብረት መዘረፋቸው ፤ ለዘመናት ከኖሩበት ቦታ እየተደበደቡ ሲሰደዱ አልፎም ሲገደሉ ማየታችን የገዢው ፓርቲ የዘረኝነት መርሕ ያስከተለው ጠንቅ መሆኑ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያላት ድርሻ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን ሀገርንና ትውልድን ወደ ከፋ ችግር የዳረገውን በዘርና በጎሳ የሚደረጉ ልዩነቶችን አለማውገዟና ይህንን አስከፊ ድርጊት ለ25 ዓመታት የሚፈጽመውን አካል አለመገሰጿ በታሪክ ከመወቀስ አያድናትም። በተለይም በቅርቡ በኦሮምያ፣ በአማራ፣ በቤንሻጉል ጉምዝ፣ ጋምቤላ፣ በአዲስ አበባ እንዲሁም በተለያዩ ክልሎች በዜጎች ላይ እየተየፈፀመ ያለውን እሥር እንግልትና ግድያ አለማውገዟና ከሕዝቡ ጋር አለመቆማ እጅግ አሳዝኖናል።

በውጪው ዓለም በስደት ላይ ላሉ ኢትዮጵያውያን በመንፈሳዊም ሆነ በማኅበራዊ አገልግሎት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተች የምትገኘው የርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እየታየ ያለውን የሀገራችንን ችግር በመመልከት ወደ ከፋ ደረጃ ከመድረሱ በፊት መንግሥት የሚወስደውን የኃይል እርምጃ በአስቸኳይ እንዲያቆም ይህንን የአቋም መግለጫ ለማውጣት ተገዳለች።

<u>የአቋም መግለጫ</u>

1ኛ፡- መንግሥት በዘርና በጎሳ ለ25 ዓመታት ሕዝቡን ከፋፍሎ የገዛበት አመራር ለማንም ስላልበጀ ይህንንም ሕዝቡ አውቆ ልዩነትን ወደ ጎን በመተው ወደ ቀደመ አንድነቱ ተመልሶ በቁጣና በብሶት ለለውጥ በአንድነት ተነስቷል። መንግሥት የሀገሪቱን ሰላም ከፈለገ ማሠር መግደል ማቆም አለበት። እስከ አሁንም በማን አለብኝነት በንጹሐን ኢትዮጵያውያን ላይ በከንቱ ያፈሰሰውን ደም አጥብቀን እናወግዛለን ።

2ኛ፡- መንግሥት በአምባገነንነት በሕዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ኢሰብዓዊ ድርጊት እያወገዝን ሕዝባችን ለሀገራችን የሚበጀውን መልካም አስተዳደር ለማምጣት የሚያደርገውን ብሔራው ትግል እንደግፋልን።

3ኛ፡- ቅዱስ ሲኖዶሱ መንግሥት በሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ በይፋ እንዲቃወም እየጠየቀን ብፁዓን አባቶች፣ የገዳማት እና የአድባራት አስተዳዳሪዎች ግንባር ቀደም በመሆን በጎሳዎች መካከል ግጭት እንዲፈጠር መንግሥት የዘረጋውን የልዩነት ሥርዓት እንዲጠፋ

ትውልዱን በማስተማር፤ በመምከርና በመገሰጽ ወደ ብሔራዊ አንድነት እንደያመጡትና የሕዝቡን ጥያቄ ጥያቄያቸው በማድረግ ከሕዝቡ ጎን እንዲቆሙ እንጠይቃለን።

4ኛ፡- ውድ ኢትዮጵያውን ወገኖቻችን በሙሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከገባችበት ቀውስ ወጥታ መንግሥት የሚሠራውን ግፍ ለማስቆም መለያየት ስለማይበጀን በአንድነት እንድንድቆም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

5ኛ፡- የፖሊስ፣ የሀገር መከላከያ ሠራዊት፡- ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሁሌም ስንቅ ከሚያቀብለው ወገኖቹ ጎን በመቆም ደሙን አፍሶ አጥንቱን ከስክሶ ከሀገሩ አልፎ የሌላን ሀገር ዳር ድንበር ሰላምና ፀጥታ ሲያስከብር የኖረ እንጂ አሁን እንደሚያደርገው የገዛ ወገኑን ጨክኖ ሲገድል ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም። ያ ታሪክ ግን ዛሬ ተቀይሮ ሕዝቡ ይጠብቀኛል ባለው ሠራዊት ያለምንም ርኅራኄ ግፍና መከራ እየደረሰበት ይገኛል። የገባችሁት ቃል ሕዝቡንና ሀገሪቱን ከጠላት ለመጠበቅ እንጂ የመንግሥትን ትእዛዝ ተቀብላችሁ ወገናችሁን ለመግደል ስላልሆነ አሁን እያደረሳችሁ ያላችሁትን ድብደባ፣ እስር፣ ግድያና ማዋከብ እንድታቆሙና ከሕዝቡ ጎን እንድትቆሙ እየጠየቅን በንጹሐን ወገኖቻችሁ ላይ እየፈጸማችሁት ያለውን ግፍ አጥብቀን እናወግዛለን።

6ኛ፡- በተለያዩ ጊዜያት በሰላማዊ መንገድ ሕዝቡ ያቀረበውን ጥያቄ ወደ ጎን በመተው መንግሥት ያለግባብ ያሰራቸውን ንጹሐን ዜጎች እንዲፈታ እንጠይቃለን።

7ኛ፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወራሪ ጠላት እንዲሁም ከተለያዩ ችግሮች እንዲድን ነገሥታት፤ የሃይማኖት መሪዎች ሀገራዊ የምህላ ጸሎት በማወጅ በእግዚአብሔር ቸርነት ሕዝቡንም ሀገሪቷንም ከክፉ ሲጠብቁ ቆይተዋል። አሁንም በሀገራችን ላይ የተፈጠረው ችግር ወደከፋ የእርስ በእርስ መጠፋፋት ሳያመራ እግዚአብሔር ሀገራችንን በሰላም፤ ህዝቦቿንም በፍቅር እንዲጠብቅልን የሃይማኖት መሪዎች በመላው ዓለም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የምህላ ጸሎት እንዲያውጁ አጥብቀን አንጠይቃለን።

እግዚአብሔር ሀገራችንን ኢትዮጵያን ይባርክ።

የርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን
ጊዜያዊ አመራር የሰላምና መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ
ዋሽንግተን ዲሲ

ግልባጭ

ለቅዱስ ሲኖዶስ
ለኢትዮጵያ መንግሥት
ለመንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት

ለጠቅላይ ቤተ ክህነት
ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት
ለዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ አህጉረ ስብከት
ለአሜሪካ መንግሥት
ለተባበሩት መንግሥታት
ለአውሮጳ ኅብረት
ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት
ለሰብአዊ መብት ድርጅቶች
ለተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች